“ሲነቅፏችሁና ሲያሳድዷችሁ በእኔም ምክንያት ክፉዉንም ሁሉ በዉሸት ሲናገሩባችሁ ብጹዓን ናችሁ። ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ፤ ሀሴትም አድርጉ ከናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያት እንዲሁ አሳድደዋቸዋልና”

ማቴ 5፥11-12

ክርስቲያኖች የክርስቶስን ባሕርይ እያንጸባርቁ በዝህች ምድር የሚመላለሱ ከሆነ ስደትና መከራ መጠላትም እንደሚደርስባቸዉ የታወቀ ነው። ክርስቶስ እራሱን እንድዚያ ካሳደዱት ተከታዮቹን እንዴት አያሳድዱም? ስለዚህም ጉዳይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር እኔን ስለጠሉ እናንተትንም ይጠሏችኋል ባሪያ ከጌታዉ አይበልጥምና ብሏል (ዮሐ 15፥18-20)። ለስደትና መከራ የተዘጋጁ እንዲሆኑ ደቀመዛሙርቱን መክሯቸዋል። በኋላም የመጡት ሐዋሪያት ስለክርስቶስ መሰደድ ታላቅ ክብር እንዳለዉና ዋጋዉም ትልቅ እንደሆነ መስክረዋል(ሥራ 5፥ 41-42)። እዉነተኛ የክርስቶስ ተከታይ ከሆንን ስለኛ መጥፎ ነገር በዉሸት መነገሩና የተለያዩ ስደቶች ሰለባ መሆናችን የማይቀር መሆኑን መገንዘብና ጠብቀን መዘጋጀት አለብን። እንዲያዉም በሃይማኖታችን በዚህች ምድር ስንመላለስ የሆነ ስደት የማይደርስብን ከሆነ ከዓለም ጋር ተጣብቀናልና ዓለምንም መስለናልና የተለያችሁ ሁኑ (ከዓለም ተለዩ) የተባለዉን ትእዛዝ አልጠበቅንምና እራሳችንን መመርመር አለብን።

ታድያ ይህም ሲባል የሚደርስብን ስደት ወይንም ስድብና ግፍያ ከራሳችን መጥፎ ባሕርይ እንዳይሆን መጠንቀቅ አለብን (1ጴጥ 4፥15-16)። በተጨማሪም ከክርስትና ዉጭ በተለያዩ ምክንያቶች(በዘር፤ በጎሳ በሌላም እምነት… ወዘተ) ብሰዎች ላይ ስደቶች ይደርሳሉ። እነዚህ ስደቶች ከተራ ስድብ ጀምሮ እስከ ሕይወት መጥፋት የሚደርሱ መሆናቸዉን በዕለት በዕለት ዜና የምንሰማና ትክክል ናቸው ብለን የምንደግፍ ባይሆንም በዝህ መጽሓፍ ቅዱስ ክፍል የተጠቀሰውን አይመለከትም ስለ ክርስቶስ ተብለው አይደለምና። ይሁን እንጂ እንደ ክርስቲያን ማንኛዉንም ግፍ ማጋለጥና መዋጋት ግዴታችህን ነው።

በዚህ ጥቅስ የምናየው ስድብና ክፉዉን በዉሸት በአማኞች ላይ መናገር እንደ ትላልቅ የስደት ዓይነቶች ከፍ ማለቱን ነው። ይህ ዓይነቱ ስደትና ግፍያ ልክ በአካል ላይ እንደሚደርስ ጥቃት፤ ከሀገር እንደመባረር፤ ንብረትን እንደ መዘረፍ እንደመሳሰሉት ይታያል። አንዳንድ ጽሁፎች እንደሚገልጹት የአፍ ነቀፌታ ክነፍስ ግዲያና ክፍትወት ኀጢአት የሚጎዳ እንደሆነ የአይሁዶች የወቅቱ ባህል ይደነግጋል። ምክንያቱም ሰው ስሙ ከጠፉ የመኖር ሕልዉናውም ይጠፉልና ከበስኋላ በሃሜት በፊት ለፊት በስድብ መልክ የሚደርሱ ነቀፌታዎች ከባድ ስደቶች ናቸው።

ሌላው የምናየው ነገር ስለ ክርስቶስ ሲባል የሚደርሱብንን ስደቶችና አለመመቸቶች በማጉረምረምና ፊትን በማጨማደድ ሳይሆን በደስታ መቀበል እንዳለብን ነው። ይህም ማለት ስደትና መከራው የደስታችን ምንጭ ነው ማለት አይደለም። ነገርግን በመከራና ስደቱ ዉስጥ ሊያሳልፈን የሚችለዉን አምላክ ዘላለማዊነት እያየን የሚደርስብን ስደትና መከራ ጊዜያዊ፤ ሽልማታችን ግን ዘላለማዊ መሆኑን እንድንገነዘብ ነው።

ለዚህም የቀደሙቱ የሃይማኖት አባቶችና ክርስቲያናት በሮማ መንግስት ጊዜና ከዚያም ወዲህ በመካከለኛዉ ክፍለ ዘመን በጽናት ያሳለፉትና የክርስትና ሃይማኖትን ያቆዩልን ምሳሌያችን ነው።

በዚህ ጥቅስ በተሰጠው ትዕዛዝ ዉስጥ በትኩረት ማየት ያለብን መከራንና ስደትን በደስታ ተቀበሉ ሀሴትም አድርጉ ሲለን ደስታችን በጣም ከፍ ያለ በመሆኑ ከሚደርስብን ሕመም የበለጠ ሆኖ እንዲታይና "እንዴት ቻሉት" እስከሚሉ ድረስ ለሌሎች ምሳሌ እንድንሆን ነው። በሚደርብን ስደት ውስጥ ማስምሰል የሌለበትና እውነተኛ የታዛዥነት ገጽታ ማሳየት ይጠብቅብናል። ስደትና ግፍያ በክርስቶስ ምክንያት በሚደርስብን ጊዜስ ለአሳዳጆቹ ምን ዓይንት ምላሽ መስጠት አለብን? ፍቅርን እንድናሳያቸው፣ እንድንጸልይላቸው እራሱ ኢየሱስ በምድር በነበረበት ጊዜ እንዳስተማረው (ማቴ 5፥ 43-48) ዛሬም ወንጌል በተለያየ መልኩ ያሳስበናል። ለዚህም እስጢፋኖስ በተወገረበት ጊዜ ያሳየው በቂ ምሳሌያችን ነው(ሐዋ 7፤59-60)።

የክፍሉ ትምህርት ለሚደርስብን ስደትና መከራ ከሰማያት ታላቅ ዋጋን እንደምናገኝ ይገልጻል። በምድር ላይ ሳለን ለክርስትናችን የሚደርስብን የቃላትም ሆኑ የሥጋ ጥቃቶች ጊዜያዊ ናቸዉ። ሕይወትም የሚታለፍበት ቢሆን በዚህች ዓለም ላይ (ስደትም ባይኖር) የምንኖረው ለአጭር ጊዜ ነው። በአንጻሩ ግን የስማያቱ ዋጋና መጭው ኑሮ ዘላለማዊ ነው። ዛሬ ታይቶ ነገ የሚጠፋ አይደለም። ለዚህም ነው ብዙዎች ሐዋሪያትና የቀድሞ ክርስቲያናት በደረሱባቸው ስደቶችና ገፍያዎች ከቦታቸው ሳይነቃነቁ ጸንተው ይህንን የፍቅርና የሰላም እምነት ያቆዩልን።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ቀደም ያሉትን ነቢያት እንዲሁ አሳደዋቸዋልና ያለው።

እንግዲህ ዛሬ በሰደት ደረጃ ክርስቲያንን በእንጨት ላይ እያሰሩ በማቃጠል እንደችቦ መብራት መጠቀም የለም። ይሁንና ዛሬም በተለያዩ ሀገሮች በተለይም የእስልምና፣ የሀንዱ...ወዘተ እምነት ተከታዮች አብላጫ በሆኑበት አካባቢዎችና መንግስት የኮሚኒስት የአስተዳደር ሥርዓት በሚያራምድባቸው አገሮች እስከ ሕይወት ማጥፋት ድረስ ግልጽ የሆነ ስደት በክርስቲያኖች ላይ ይደርሳል።

ዲሞክራሲ በገነነባቸዉ በአሜሪካና አዉሮፓስ? በርግጥ ከላይ የተጠቀሱት ግልጽ ስደቶች በነዚህ ህብረተሰቦች ዉስጥ አይታይም-- ስለሆነም እግዚአብሔርን ይመስገን። ይሁን እንጂ ሰደት መልኩን ቀይሮ ክርስቲያኖች እራሳቸዉን በግልም ሆነ ቤተሰቦቻቸዉን እንዳይመሩ፣ እምነታቸዉን በአደባባይ፣ በትምህርት ቤት፣ በህግ ቤቶች እንዳይገልጹ እንዲሁም ያላቸዉን ፕችንስፕሎች እያመቻመቹ(compromise) እንዲኖሩ የተለያዩ ባህላዊ ልምዶችና ህጋዊ ማነቆዎች ከፍ ያለ ተጽዕኖዎች ያደርጋሉ።

ስለዚህ በክርስትያንነታችን የተልያዩ ተግዳሮቶች እንደሚገጥሙን በማወቅና እንደቃሉ ትምህርት በመመራት አይናችንን በዋናው ሽልማት ላይ በማተኮር እንመላለስ።

ለዚህም የሰማይና የምድር ፈጣሪና ጌታ ይርዳን! አሜን።